የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No. 25
ADDIS ABABA 25[th] March 2011

ማውጫ

CONTENTS

ደንብ ቁጥር ፻፺፱/፪ሺ፫

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.........ገፅ ፭ሺ፯፻፸፩

Regulation No.199/2011

Technical and Vocational Education and Training Agency Establishment Council of Ministers Regulation. ....Page 5771

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፱/፪ሺ፫**

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፱/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ማሰልጠኛ ተቋም" ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ላይ የተሰማራ የመንግሥት፣ የግል ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ነው፤

፪. "የትብብር ሥልጠና" ማለት የማሰልጠኛ ተቋሞችና የልማት ድርጅቶች በትብብር የሚሰጡት ሥልጠና ነው፤

፫. "የሙያ ብቃት ምዘና" ማለት ተፈላጊ ብቃት ላይ የተደረሰ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚከናወን ማስረጃ የማሰባሰብና በተገኘው መረጃ መሠረት ተፈላጊው ብቃት መያዙን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

፬. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፭. "ሚኒስቴር" ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ነው፤

**Council of Ministers Regulation No. 199/2011**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF TECHNICAL AND VOCATIONAL EDUCATION AND TRAINING AGENCY**

This Regulation is issued by the Council of Ministers in accordance with Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

**1. *Short Title***

This Regulation may be cited as the "Technical and Vocational Education and Training Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 199/2011".

**2. *Definitions***

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1. "training institution" means a public, private or non-governmental institution engaged in the provision of technical and vocational education and training;

2. "cooperative training" means a mode of training delivery that is provided under the cooperation of training institutions and enterprises;

3. "occupational competency assessment" means the process of collecting evidence and making judgments on whether competence has been achieved;

4. "Regional State" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

5. "Ministry" means the Ministry of Education;